COLORADO
Governor Jared Polis

Translation provided by Office of International and Immigrant Affairs

# D 2020 012

**አስፈፃሚ ትዕዛዝ**

**በኮቪድ-19 ለተጎዱት ኮሎራዶአዊያን እፎይታ ለመስጠት ከኪራይ ቤት ማስለቀቆችን፣ የቤት መውረሶችን እና የህዝብ መገልገያዎችን ማቋረጥን መገደብ እና የሥራ አጥነት የኢንሹራንስ ክፍያ የይገባኛል ጥያቄ ሂደት ማፋጠን ትዕዛዝ**

በኮሎራዶ ግዛት ገዢ ጽ/ቤት በተሰጠው ስልጣን መሠረት በማድረግ በተለይም በኮሎራዶ ህገ-መንግስት አንቀጽ 4 ክፍል 2 እና አግባብነት ባላቸው የኮሎራዶ የአደጋ ጊዜ ድንገተኛ ድንጋጌን C.R.S. § 24-33.5-701, *et seq. (Act)* መሠረት በማድረግእኔ ጄሬድ ፖሊስ የኮሎራዶ ግዛት ገዢ ከኮሮና ቫይረስ በሽታ 2019 (ኮቪዲ-19) የተነሳ በኮሎራዶ ውስጥ አሁን ያለውን የኢኮኖሚ ቀውስ ለማቃለል፣ ምላሽ ለመስጠት እና ለማገገም፤ ከኪራይ ቤት ማስለቀቆችን፣ የቤት መውረሶችን እና የህዝብ መገልገያዎችን ማቋረጥን የሚገድብ እና የሥራ አጥነት የኢንሹራንስ ክፍያ የይገባኛል ጥያቄ ሂደት የሚያፋጥን ይህንን የሥራ አስፈፃሚ ትዕዛዝ እሰጠዋለሁ።

## I. <u>ዳራ እና ዓላማ</u>

መጋቢት 5 ቀን 2020 የኮሎራዶ የህዝብ ጤና እና የአካባቢ ጥበቃ (CDPHE) የህዝብ ጤና ላብራቶሪ በኮሎራዶ ውስጥ የመጀመሪያውን የተገመተ አዎንታዊ የ ኮቪድ-19 ምርመራ ውጤት አረጋግጧል። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የተረጋገጡ ጉዳዮች ቁጥር እየጨመረ መሄዱን የቀጠለ ሲሆን በመላ ግዛቱ ውስጥ የህብረተሰብ ስርጭት የሚያሳይ መረጃ አለን። በመጋቢት 10 ቀን 2020 የአደጋ ጊዜ ድንገተኛ ሁኔታ በቃል አውጃለሁ እናም የሚዛመደውን የአስፈፃሚ ትዕዛዝ D 2020 003 በመጋቢት 11 ቀን 2020 ሰጥቻለሁ።

የእኔ አስተዳደር ከሌሎች የግዛት፣ አካባቢያዊ እና ከፌዴራል ባለስልጣናት ጋር በመሆን የወረርሽኙን ጉዳቶች ለመቀነስ፣ ተጨማሪ መስፋፋትን ለመከላከል እና የጤና እንክብካቤ ሀብቶቻችንን እንዳያጥለቀልቁ ለመከላከል በርካታ እርምጃዎችን ወስዷል።

ኮቪድ-19 ያለው ኢኮኖሚያዊ ተፅእኖ ከፍተኛ ነው እናም የብዙ ኮሎራዳውያን እና የአከባቢ ንግዶችን የኢኮኖሚ መረጋጋትን አደጋ ላይ ይጥላል። በኮቪድ-19 የቀረበው የብክለት አደጋ የብዙ ንግዶች መዘጋት አስፈላጊ እንዲሆን አድርጓል። በሁሉም ማለት ይቻላል የኢኮኖሚ ዘርፎች ውስጥ ያሉ አሠሪዎች እና ሰራተኞች ላይ ከባድ ጉዳት ደርሰዋል። የኢኮኖሚ ደህንነትን፣ የስራ ስምሪትን፣ የህብረተሰቡ መተባበርን እና የህብረተሰቡ ማገገምን ለመደገፍ እርምጃ መውሰድ አለብን።

በዚህ የሥራ አስፈፃሚ ትእዛዝ ለጊዜው ከኪራይ ቤት ማስለቀቆችን፣ የቤት መውረሶችን እና የህዝብ መገልገያዎችን ማቋረጥን እየገደብኩ እና በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ለተጠቁት ኮሎዶአዊያን ሥራ አጦች እገዛ እያቀረብኩ ነው። በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ከተከሰተው ወቅታዊ ኢኮኖሚያዊ ቀውስ ለመቀነስ፣ ምላሽ ለመስጠት እና ለማገገም ጥረቶችን ለማሻሻል እና ለማፋጠን የግዛቱን ሀብቶችን የበለጠ በማንቀሳቀስ ላይ ነኝ። ይህ የሥራ አስፈፃሚ ትዕዛዝ በሚቀጥሉት ሳምንቶች እና ወራቶች ውስጥ የኮሎራዶ ማህበረሰቦችን እና የንግድ ድርጅቶችን ኢኮኖሚያዊ ደህንነት ለመጠበቅ ይረዳል።

## II. <u>የቤት መዉረስ እና ከኪራይ ቤት የማስለቀቅ መመሪያዎች</u>

A. እስከ ሚያዝያ 30 ቀን 2020 ድረስ ያለ ምክንያት ወይም ከኪራይ ክፍያ መዘግየት ወይም አለመክፈል ወይም ከአነስተኛ የተከራይነት ህግን መጣስ የተነሳ ተከራዮችን ወይም የተንቀሳቃሽ ቤት ባለቤቶችን ከማስወጣት ወይም የቤት ማስለቀቅን ሂደቶችን እነሱ ላይ መፈጸምን ለማስወገድ ማንኛውንም ሕጋዊ እርምጃ ለመለየት ከንብረት ባለቤቶች እና ከአከራዮች ጋር እንዲሰሩ የአከባቢያዊ ጉዳዮች መምሪያ (DOLA)፣ የሠራተኛና የስራ ቅጥር መምሪያ (CDLE) እና የቁጥጥር አካላት ኤጀንሲዎች (DORA) ዋና ሥራ አስፈፃሚ ዳይሬክተሮችን እመራለሁ። እንዲሁም ዋና ስራ አስፈፃሚ ዳይሬክተሮች ለተከራዮች እና ለተንቀሳቃሽ ቤት ባለቤቶች ዘግይቶ ለሚከፈል ወይም ለማይከፍል ክፍያ ወጪ ወይም ቅጣት እስከ ሚያዚያ 30 ቀን 2020 ድረስ ነጻ ለማድረግ ከንብረት ባለቤቶች እና ከአከራዮች ጋር አብረው ይሰራሉ።

B. የክልል እና የአካባቢ ኤጀንሲዎች ሀብትን ለመጠበቅ እና ቅድሚያ ለመስጠት እና ለኮቪድ-19 ወረርሽኝ ምላሽ አስፈላጊ ተግባራትን ለማከናወን የሕግ አስከባሪ መኮንኖች እንዲገኙ ለማድረግ የሕዝብ ደህንነት መምሪያው (DPS) ዋና ሥራ አስፈፃሚ እንደዚህ ያሉ እርምጃዎች የህዝብን ጤና እና ደህንነት ለመጠበቅ አስፈላጊ ካልሆኑ በስተቀር የመኖሪያ ማስለቀቅ እንቅስቃሴን በግዛቱን ውስጥ እስከ ሚያዚያ 30 ቀን 2020 ድረስ ለማስቆም ከህግ አስከባሪ ኤጀንሲዎቻቸው ጋር ተመሳሳይ መደበኛ እርምጃዎችን እንዲወስዱ ከሁሉም የፖሊስ መኮንኖች፣ ከንቲባዎች እና ሌሎች የአካባቢ መሪዎች ጋር እንዲሠራ እመራለሁ።

C. ከኮቪድ-19 ጋር በተያያዘው ኢኮኖሚያዊ ቀውስ ምክንያት የገንዘብ ችግር ላጋጠማቸው ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ቤተሰቦች የአጭር ጊዜ ኪራይ እና የቤት ብድር (ሞርጌጅ) ድጋፍ ለመስጠት እና እርዳታውም ቀጣይነት ያለው የቀድሞ የሥራ ታሪክ ላላቸው እና ከCDPHE ወቅታዊ ወይም የወደፊቱ የኮቪድ-19 የህዝብ ጤና ትዕዛዛት ጋር በተያያዘ ሥራ ላጡ ቅድሚያ በመስጠት ድጋፍ እንዲያቀርብ ከአደጋው ጊዜ አስቸኳይ ፈንድ ሶስት ሚሊዮን ዶላር ($3,000,000) በመወሰድ ለDOLA እንዲገኝ አዛለሁ። እነዚህ ፈንዶች ይህ የሥራ አስፈፃሚ ትእዛዝ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለስድስት (6) ወራት የሚቆዩ ሲሆን ማንኛውም ጥቅም ላይ ያልዋለ ገንዘብ በአደጋ ጊዜ አስቸኳይ ፈንዱ ውስጥ ይቆያል። በፌዴራል መንግሥቱ የሚተኩ ፈንድዎች ወደ የአደጋ ጊዜ አስቸኳይ ፈንድ ይመለሳሉ። ጊዜያዊ የኪራይ እና የቤት ብድር (የሞርጌጅ) ድጋፍን ክፍፍልን በስራ ላይ ለማዋል DOLA በተጨማሪ ለትርፍ ካልሆኑ እና ከአከባቢ መንግስት አጋሮችን ጨምሮ ከግዛት አቀፍ አጋሮች ጋር እንዲሠራ እመራለሁ። ይህንን መመሪያ በሚፈፀምበት ጊዜ DOLA ግለሰቦች ጥቅሞችን ሁለቴ ማግኘት አለመቻላቸውን ያረጋግጣል።

D. በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ምክንያት የገንዘብ ችግር ያጋጠሙዋቸውን ነዋሪዎችን ፍላጎት ለመገምገም የሚከራዩ ቤቶችን ወይም ማቆሚያዎችን ለዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ቤተሰቦች የሚያቀርቡ የብዙ ቤተሰብ መኖሪያ ቤቶችን እና የተንቀሳቃች ቤት ማቆሚያዎች ባለንብረቶች ጋር እንዲሠራ ለDOLA መመሪያ እሰጣለሁ እንዲሁም ለኮሎራዶአዊያን የመኖሪያ እና የመጠለያ ፍላጎቶችን

ለመጠበቅ የሚረዱ ያሉ ወይም ሊገኙ የሚችሉ ፌዴራል፣ ግለሰቦች እና የበጎ አድራጎት የገንዘብ ድጋፍ ምንጮችን ጨምሮ
ነገር ግን በእነዚህ ሳይገደብ የኪራይ ኪሳራዎችን ለመሸፈን የሚረዱ ዘዴዎችን እንዲገመግም ለDOLA መመሪያ እሰጣለሁ። ይህንን መመሪያ በሚፈፀምበት ጊዜ DOLA ግለሰቦች ጥቅሞችን ሁለቴ ማግኘት አለመቻላቸውን ያረጋግጣል።

E. ጊዜያዊ የኪራይ እና የቤት ብድር (ሞርጌጅ) ዕርዳታን ለማሰራጨት ውሂቦችን እንዲያጋሩ እና መመሪያዎችን እና ሂደቶችን እንዲያሻሽሉ DOLA እና CDLE መመሪያ እሰጣለሁ።

F. የመኖሪያ እና የንግድ ቤት መወረስ እባ የግለሰቦች እና የአነስተኛ ንግዶች መፈናቀልን አደጋዎችን ለመዋጋት ልምዶችን እና ፖሊሲዎችን ለመለየት በባንክ ክፍሎች እና በፋይናንስ አገልግሎቶች በኩል በመንግስት ከተሰጡት የፋይናንስ ተቋማት ጋር እንዲሰራ ለDORA መመሪያ እሰጣለሁ። በተጨማሪም የቤት መወረስ እና ከቤት መወረስ ጋር የተያያዙ ከቤት ማስለቀቆች ከኮቪድ-19 ወረርሽኝ ተፅእኖዎች ምክንያት የቤተሰብ እና የንግድ ገቢ ከፍተኛ ቅነሳ ሲነሳ የመኖሪያ እና የንግድ ቤት ብድር (ሞርጌጅ) የሚዪዙ ባንኮችን፣ የብድር ማህበራትን እና ሌሎች የገንዘብ ተቋማትን የቤት መውረሶችን እና ከቤት ማስለቀቆችን እንዲያቆሙ ለማበረታታ እርምጃዎችን እንዲወስድ ለDORA መመሪያ እሰጣለሁ። በተጨማሪም በኮቪድ-19 ምክንያት ኢኮኖሚያዊ ተፅእኖ ለደረሰባቸውን ደንበኞች እና ንግዶች የመኖሪያ እና የንግድ ቤት ብድር (ሞርጌጅ)፣ ብድሮች፣ የመኪና ብድሮች እና የተማሪ ብድሮች እና አነስተኛ የንግድ ብድሮችን ጨምሮ ለሁሉም የሸማች ብድሮች የክፍያ ዘጠና (90) ቀናት ማራዘሚያ እንዲሰጡ እነዚህ የገንዘብ ተቋማትን እንዲያበረታታ ለDORA መመሪያ እሰጣለሁ።

G. ሁሉም የኳውንቲ ጸሃፊዎች እና መዝገብ ያዦች የመኖሪያ ወይም የንግድ ብድር የማጣራት ሂደት እንደሚጠናቀቅ ለማረጋገጥ ሁነቶችን እና ሌሎች ተዛማጅ ሰነዶችን በመመዝገብ በእውነተኛ ንብረት ውስጥ እውነተኛ ትርፎችን ለማስጠበቅ ለሚፈልጉ የፋይናንስ ተቋማት፣ እስከተቻለው የተቻለ መጠን ድረስ ቀጣይነት አገልግሎት እንዲያቀርቡ መመሪያ እሰጣለሁ።

H. የኮሎራዶን ግዛት የህዝብ ባለአደራዎች የቤት መውረስ ሂደትን በሚመለከት የወጡት የኮሎራዶን የተከለሱ ህግች ርዕስ 38 አንቀጽ 38 የሚከተሉትን ድንጋጌዎች ተግባራዊነት ለ30 ቀናት ለማገድ እርምጃ እንዲወስዱ ስልጣን እሰጣለሁ፡ § 38-38-
102 (የምርጫ እና ለሽያጭ የሚቀርብ ማስታወቂያ የመቅዳት የጊዜ ገደቡን በሚመለከት)፤ § 38-38-103 (የተቀናጀ ማስታወቂያ ለመላክ ቀነ-ገደቡን በሚመለከት)፤ § 38- 38-104 (አንድ ወገን ለመፈፀም የህሳብ ማስታወቂያ ለማስገባት ያለው የጊዜ ማገደብ እና አንድ ባለአደራ ማስታወቂያውን ለጽሑፍ ማስታወሻው ያዡ ወይም ለጠበቁ መላክ ያለበት የጊዜ ወሰን፣ እና ለመፈወስ ገንዘብ ለማሰባሰብ የጊዜ ገደቡን በሚመለከት)፤ § 38-38-302 (የዋጋ ማቅረቢያ ገንዘብን የጊዜ ቀነ-ገደብ በሚመለከት)፤ እና § 38-38-501 (የማረጋገጫ ተግባር ለመፈፀም እና ለመመዝገብ ቀነ-ገደቡን በሚመለከት)። እነዚህን ማራዘሞች በተመለከተ በአንድ የህዝብ ባላአደራ የሚደረጉ ማንኛውም እርምጃዎች በባላደራው ድህረ-ገጽ ላይ፣ በኤሌክትሮኒክ ደብዳቤ (ከተቻለ) እና በራስ-ሰር መልእክቶች መገኘት እንዲቻል ይደረጋል

I. በዘገየ የግብር ክፍያዎች ምክንያት በ § 39-10-104.5 ድንጋጌዎች መሠረት ሊካተት የሚችል ልዩ ወለዶች ለማገድ ወይም ለመተው እርምጃ እንዲወስዱ በኮሎራዶ ግዛት ለካውንቲ ገንዘብ ያዥዎች ፈቃድ እሰጣለሁ። እነዚህን እርምጃዎን በተመለከተ በአንድ ገንዘብ ያዥ የሚደረጉ ማንኛውም እርምጃዎች በገንዘብ ያዡ ድህረ-ገጽ ላይ፣ በኤሌክትሮኒክ ደብዳቤ (ከተቻለ) እና በራስ-ሰር መልእክቶች መገኘት እንዲቻል ይደረጋል።

J. ለዚህ አስፈፃሚ ትእዛዝ ዓላማ “ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ቤተሰቦች” ማለት ከአከባቢው መካከለኛ ገቢ 50 በመቶ በታች የሆኑ ቤተሰቦች ማለት ነው።

K. በዚህ አስፈፃሚ ትእዛዝ ውስጥ ያለ የትኛውም ነገር የተከራይን የቤት ኪራይ የመክፈልን ግዴታ አይገታውም ወይም የአከራዩ የደረሰ የቤት ኪራዩን የማስመለስ አቅሙን አይገድብም፣ ወይም ደግሞ ከህዝብ ጤና እና ደህንነት መስፈርቶች ወይም ከሌሎች የህግ መስፈርቶች ጋር አይጣጣምም።

## III. <u>*የመገልገያ መመሪያዎች*</u>

A. በኮቪድ-19 ተፅእኖዎች ጋር ተያይዞ ከመኖሪያ እና አነስተኛ የንግድ ሥራ ደንበኞች ለዘገየ ወይም ላለተከፈለ ክፍያ የአገልግሎት መቋረጥን ለማገድ በግዛቱ ውስጥ ከሚገኙት የህዝብ መገልገያዎች ሁሉ ጋር እንዲሠራ በ DORA ውስጥ ላለው የህዝብ መገልገያ ኮሚሽን (PUC) መመሪያ እሰጣለሁ።

B. በተጨማሪም በኮቪድ-19 ተጽዕኖዎች በጣም ጫና ለተፈጠረባቸው ለሁሉም የመኖሪያ ደንበኞች እና አነስተኛ የንግድ ሸማቾች የመቀጠያ ክፍያዎችን ለማስቀረት እና የዘገየ ክፍያ ወጪዎች መከማቸትን ለማገድ ከሁሉም የህዝብ መገልገያዎች ጋር እንዲሰራ እንዲሁም ባለመክፈርል ወይም ከኮቪድ-19 ተጽዕኖዎች ጋር በተዛመደ ወደኋላ መቅረት ምክንያት በአሁን ጊዜ ግንኙነት ተቋርጦባቸው ላሉ ደንበኞች አገልግሎቱን ወደነበረበት ለመመለስ ምክንያታዊ ጥረቶችን እንዲያደርግ PUCን አዘዋለሁ።

C. ከኮቪድ-19 ተጽዕኖዎች ጋር በተዛመደ ደንበኞች በተለይም ለዝቅተኛ ገቢ ኃይል ድጋፍ መርሃግብር ብቁ ለሆኑ ደንበኞች የፍጆታ ክፍያዎቻቸውን በመክፈል ለመርዳት የክፍያ እገዛ መርሃግብር ለመመስረት እና ለማቅረብ ከሁሉም የህዝብ መገልገያዎች ጋር አብሮ እንዲሠራ PUC በተጨማሪ አዛለሁ።

D. የክፍያ ድጋፍን ቅድሚያ አሰጣጥን በተመለከተ መመሪያን ለማቅረብ ከህዝብ መገልገያዎች ጋር እንዲሠራ PUCን በተጨማሪ አዛለሁ። በተጨማሪም PUC ለዚህ አስፈፃሚ ትእዛዝ ምላሽ የተወሰዱ የግዛት አቀፍ እርምጃዎች አፈፃፀም ላይ ከህዝብ መገልገያዎች ጠቃሚ ውሂቦችን

ይሰበስባል እና ይቆጣጠራል እናም በየሳምንቱ እነዚህን ጥረቶች ለገዢው ጽ/ቤት ሪፖርት ያደርጋል እና በPUC ድህረ-ገጽ ላይ ይለጠፋል።

E. ከኮቪድ-19 ጋር የተዛመዱ ተጽዕኖዎችን ለመገምገም እና ከኮቪድ-19 ጋር የተዛመዱ ጉዳቶችን ለማቃለል ለገዥው ጽ/ቤት ጠቃሚ ምክረ-ሃሳቦችን ሪፖርት ለማድረግ የኮሎራዶ የኋይል ጽ/ቤት ከአገልግሎት ሰጭዎች፣ ከንግድ ማህበራት እና በመላው ግዛቱ ካሉ የፕቶፔን ማሞቂያ ተጠቃሚዎች ጋር እንዲሠራ አዛለሁ።

F. ለዚህ አስፈፃሚ ትእዛዝ ዓላማ "ትናንሽ የንግድ ሸማቾች" ማለት በPUC በተቋቋመው የፍጆታ ታሪፍ መሠረት የፍጆታ አገልግሎቱ እንደ አነስተኛ ንግድ ተጠቃሚ ተብሎ የተመደበ የህዝብ መገልገያ ደንበኛ
ወይም እንደዚ ያለ የታሪፍ ሁኔታ እየፈለገ ያለ የህዝብ መገልገያ ደንበኛ ማለት ነው።

G. ለዚህ አስፈፃሚ ትእዛዝ ዓላማ "የሕዝብ መገልገያ" ወይም "የሕዝብ መገልገያዎች" ማለት በኮሎራዶ ግዛት ውስጥ የኤሌክትሪክ፣ ጋዝ ወይም የውሃ አገልግሎትን የሚሰጡ ባለሀብት በባለቤትነት የተያዙ፣ የማዘጋጃ ቤት ወይም የህብረት ሥራ አካላት ማለት ነው።

## IV. <u>የሥራ አጥነት ዋስትና መመሪያዎች</u>

A. የግዛቱን ኢኮኖሚያዊ መረጋጋት ለማበረታታ ለየስራ አጥነት ዋስትና(UI) ጥቅሞች ለሚያመለክቱ ግለሰቦች አገልግሎቶችን ለማሻሻል እና ለማፋጠን ከየአደጋ ጊዜ አስቸኳይ ፈንድ አንድ ሚሊዮን ዶላር ($1,000,000) እንዲወሰድ እና ለCDLE እንዲገኝ አዛለሁ። እነዚህ ፈንዶች ይህ የሥራ አስፈፃሚ ትእዛዝ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለስድስት (6) ወራት ለዚሁ አለማ የሚቆዩ ሲሆን ማንኛውም ጥቅም ላይ ያልዋለ ገንዘብ በአደጋ ጊዜ አስቸኳይ ፈንዱ ውስጥ ይቆያል። በፌዴራል መንግሥቱ የሚተኩ ፈንዶች ወደ የአደጋ ጊዜ አስቸኳይ ፈንድ ይመለሳሉ።

B. በኮቪድ-19 ተጽዕኖዎች ምክንያት የተፈናቀሉ ሰራተኞች በተቻለ መጠን ድረስ ያስገቡት የተጠናቀቀ ማመልከቻዎቻቸው በደረሰ በአስር (10) ቀናት ውስጥ ክፍያ መቀበል መጀመራቸውን ለማረጋገጥ ሲባል CDLE የUI ጥቅማጥቅሞችን የይገባኛል ሂደትን እና የክፍያን ማስራጨት ያፋጥናል።

C. IV.A. እና IV.B. መመሪያዎችን ለማከናወን ከዚህ በታች ያለውን መስፈርት አግዳለሁ፡

i. C.R.S. § 8-73-107(1)(d) የUI ጥቅም ተቀባዮች ጥቅማጥቅሞችን ከማግኘታቸው በፊት ያልተከፈለ የጥበቃ ሳምንት ያገለግላሉ እና C.R.S. § 8-73-107(1)(g)(l) የUI ጥቅም ተቀባዮች በንቃት ሥራ እንደሚፈልጉ።


ii. C.R.S. § 8-73-108(e) የ UI ጥቅሞች ለአሠሪ ተሞክሮ ደረጃ አሰጣጥ ሂሳቦች እንዲከፍሉ ይደረጋሉ እና (COVID-19) ተጽዕኖ ጋር ተያይዞ ለሚነሱ የይገባኛል ጥያቄዎች
ጥቅማጥቅሞችን በየስራ አጥነት ዋስትና ክፍል በኩል ከፈንዱ እንዲከፍል እንዲያደርግ እንጂ ከአሠሪ ተሞክሮ ደረጃ አሰጣጥ ሂሳቦች እንዳያደርግ ከCDLEን አዛለሁ።

iii. C.R.S. § 8-74-102(1) የCDLE ሰራተኞች አንድ የUI ጥቅማጥቅሞችን የይገባኛል ጥያቄ ሲደርሳቸው ለሌሎች ፍላጎት ላላቸው ወገኖች እንዲያሳውቁ እና ለተባለው ጥያቄ ጥቅማጥቅሞችን ለመስጠት ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት CDLE እንደነዚህ ያሉ ወገኖች ለቀረበላቸው ጥያቄ መልስ ለመስጠት አሥራ ሁለት (12) የቀን መቁጠሪያ ቀናት ይሰጣቸውዋል፣ እናም
ፍላጎት ላላቸው ወገኖች ማስታወቂያዎችን ከማቅረብ እና አፋጣኝ የጥቅማጥቅሞችን ክፍያን ለማረጋገጥ እንደአስፈላጊነቱ እውነታን ከመፈለግን ከማስቀደም በፊት በኮቪድ-19 ተጽዕኖ የሚነሱ የUI ጥቅማጥቅሞችን ክፍያ በሥራ አጥነት ዋስትና ክፍል በኩል ቅድሚያ እንዲሰጡ CDLE አዛለሁ።

iv. በC.R.S. § 8-74-102(1) ውስጥ በተሰጡት ስልጣናት መሠረት የCDLE ዋና ስራ አስፈፃሚ ዳይሬክተር የዚህን አስፈፃሚ ትዕዛዝ IV.A - IV.C መመሪያዎችን ለማከናወን አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጆችን ያወጣል።

## V. <u>የጊዜ ቆይታ</u>

በተጨማሪ የአስፈፃሚ ትእዛዝ ካልተራዘመ በስተቀር ይህ አስፈፃሚ ትእዛዝ ከመጋቢት 20 ቀን 2020 ጀምሮ ከሠላሳ (30) ቀናት በኋላ ከስራ ውጪ ይሆናል ነገር ግን በክፍል II.C. እና IV.A. የተገለጹት ፈንዶች ይህ አስፈፃሚ ትእዛዝ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ለስድስት (6) ወራት ለተገለፁት ዓላማዎች እንደተገኘ ይቆያሉ።



በእጄ እና በኮሎራዶ ግዛት ስራ አስፈጻሚ ማህተም ስር በዚህ 20ኛው የመጋቢት 2020 ቀን የተሰጠ።

ጃሬድ ፖሊስ
ገዢ